# ዓላማው

የዚህ መንፈሳዊ ተቋም ዓላማው ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌሉ ያስተማረውን የሰው ልጅ ሁሉ ይማረውና ይጠብቀው ዘንድ ነው። "በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ" ማቴ 10፥27 ብሎ አሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት (ሐዋርያት) እንዳዘዛቸው በአካልም በጊዜው ባለው የመገናኛ መንገድም ተጠቅመን የሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ለሰማያዊ መንግሥት በንስሐ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ነው።

ዓላማችን በዚህ ወቀት ሰዎች ፦ በኀጢአተኝነት እንደገዛ ምኞታቸው የሚሄዱበት፣ ዘባቾች የሚሆኑበት፣ ሥጋዊ ሥራን በመሥራት ከአምላካቸው የሚለዩበት፣ ክርስቶስ በደሙ የመሠረታትን ቀጥተኛይቱን እምነት የሚክዱበት፣ አስተሳሰባቸው ምድራዊ ብቻ የሚሆንበት የመጨረሻ ዘመን በመሆኑ ከዚህ ሁሉ ርቀው በተቀደሰ ሃይማኖታቸው እነዲጸኑና እንዲተጉ ተቀዳሚ ዓላማው ነው። "እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ" ይሁዳ -ቁ- 20

ሰው በእግዚአብሔር ፍቅር ሲመላለስ ሕጉን በመጠበቅ ይኖራል። ትዕዛዛቱም እርስ በእርሳችን እንዋደድ ዘንድ ነው። እርስ በእርሳችን ስንዋደድ ስንፋቀር እንተሳሰባለን እንረዳዳለን ስለዚህም ቀጣይ ዓላማችን ለተቸገረ ለተጨነቀ ሁሉ መድረስ ነው ይልቁንም ለክርስቲያን ወገኖች። በዚህም የተቀደሰ ተግባራችን የኢትዮጵያ ገዳማት በአንደኛ ደረጃ ይታሰባሉ። አሳባችንም እየተፈፀመ ነው። "ለቅዱሳንም ገንዘብ ስለ ማዋጣት ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ደነገግሁት እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ" 1ቆሮ 16፥1

ስለዚህ የዚህ መንፈሳዊ ማዕከል ከፍተኛ ትኩረቱ ሰዎች ለነፍሳቸውም ለሥጋቸውም ድህነት ያገኙ ዘንድ ነው። ለዚህ የእግዚአብሔር ኃይልና ብርታት የእመቤታችን ምልጃ አይለየን አሜን!

# ዕቅድ

- በሚቻለው አቅምና በተገኘው መንገድ ሁሉ የመንግሥቱን ወንጌል ለዓለም ሁሉ መስበክ
- በመጀመሪያይቱና በቀጥተኛይቱ ጌታ በደሙ በመሠረታት ሃይማኖት ይመራ ዘንድ ለሰው ሁሉ የተደበቀ ምሥጢርን መግለጽ
- የሰው ልጅ ሁሉ እግዚአብሔርን በማምለክ እንዲኖር ለቅዱሳንም የሚገባቸውን ክብር ይሰጥ ዘንድ እንዲያውቅ ማድረግ
- የሰው ልጅ ሁሉ ነፍስንም ስጋንም ከሚያረክሱና ከሚያቆሽሹ ኃጢአትና አጉል ሱሶች ርቆ ጤናማ ዜጋ እንዲሆን መጣር
- እውነተኛውን የወንጌል ትምህርት አውቆ ለሌሎችም ይመሰክር ዘንድ ብቁ ማድረግ
- ጥንታዊ የሆኑ ገዳማትን መደገፍ መነኮሳትና ደቀመዝሙራትን መርዳት
- የአብነት ትምህርት ቤቶችን፣ የመጽሐፍት ቤትን መገንባት፣ እድሳት የሚያስፈለጋቸውን አብያተ ክርስቲያናት ጭምር መሥራት
- እንዳስፈላጊነቱ በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን ከችግር አውጥቶ ሠርተው ይኖሩ ዘንድ መርዳት
- ከላይ የዘረዘርናቸውና ሌሎችንም ዕቅዶች በታላቁ አምላካችን በእግዚአብሔር ፈቃድ ለመከወን ሁላችን በአንድ ልብ መነሳት።